ማስታወሻ ለኢዴሃህ - ስለ ተግባራዊነት አንዳንድ ሃሳቦች

የትግላችን አቅጣጫና ህዝባችንን መልሰን የትግሉ መአከል ለማድረግ የምናነሳቸው አጀንዳዎችና የምናነግባቸው መፈክሮች በግንቦት ቅልበሳ ሳቢያ በፖለቲካው ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚና ማህበራዊ መስኮች በተከተሉትና ህዝባችንን አስከፊ የህልውና ቀውሶች ውስጥ በጣሉት የቅልበሳው መዘዞች ዙሪያ መሆን ይኖርባቸዋል ብለናል። በኛ ግምት የሃገራችን ዴሞክራቶች ከእንግዲህ ምንም አይነት የጋራ የትግል ስብስብ ከመፍጠራቸው በፊት ስለ ትግሉ አጀንዳና መፈክሮች በዚህ መልክ ስምምነት ሳይደርሱ በደፈናው " ያለውን መንግስት በጋራ ትግል አስወግዶ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ወቅት መክፈት" በሚለው አካሄድ መቀጠላቸው ብቻውን የትም የሚያደርስ አይደለም።

የትግል ስትራቴጂያችንን ስንነድፍ ከወዲሁ ዛሬ በህብረተሰቡ ውስጥ አደገኛ የሆነ የትጥቅ መፍታትና የጨለምተኝነት አባዜ እንደሰፈነ ተረድተን ይህንንም ስሌት ውስጥ አስገብተን መሆን ይኖርበታል። ይህንን ለማድረግና ወደ ህዝባችን ለመድረስ የቅድሚያ ቅድሚያ ተግባራችን "አንቀሳቃሽ ሃይል" የምንለው ማለትም በውጭም በሃገር ውስጥም በግንቦትና ከዚያም በቀደሙት አመታት ለዴሞክራሲያዊ ለውጥ ሲታገል የነበረው ግንባር ቀደም ሃይል በዚህ ስትራቴጂ አምኖና በነዚህ መፈክሮች ዙሪያ ተደራጅቶ እንዲታገል የተቻለውን ሁሉ መስራት ይሆናል። ለዚህ ደግሞ የአጭርና የረዥም ጊዜ እቅድ ያስፈልገናል፡

## ሀ/ የአጭር ጊዜ አካሄዳችን።

1. የህብረቱን **የድጋፍ ኮሚቴዎች ማጠናከርና** የዚህ አዲሱ ስትራቴጂያችን አራማጅ ሃይሎች የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት። እርግጥ ይህ ህዝባችንን መልሶ የትግሉ ማእበል አድርጎ የመታገል ያህል ቁም ነገር በአንድ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች ስብስብ አማካኝነት ብቻ ሊከናወን አይችልም። ይህም ሆኖ የዴሞክራቶች የጋራ የትግል መድረክ እስኪፈጠርና እንዲያውም ይህ እንዲፈጠር በኛ በኩል የራሳችንን የቤት ስራ መስራት ማለትም የድጋፍ ኮሚቴዎቻችንን በማደራጀትና ይህንን አቋማችንን በያሉበት ለተደራጁም ሳልተደራጁም ዜጎች በማስተዋወቅ በተጨባጭ ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚሰሩበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል። ይህንን እውን ለማድረግ ለሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ያስተላለፍነውን ሰነዳችንን ለነሱም አሰራጭተን እንዲወያዩበትና ተግባራዊነቱን በተመለከተ በአውሮፓና አሜሪካ ስብሰባዎች እንዲደረጉ መስራት ይኖርብናል ማለት ነው።

2. ይህ ተግባር መልክ እንደያዘ ቀጣዩ ስራ **የህብረቱን ሸንጎ መጥራትና** የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን የነዚህ የድጋፍ ኮሚቴዎች ተወካዮች እንዲገኙ ማድረግ ይሆናል። ለዚህም ከህብረቱ አመራር በሁለቱ አህጉሮች ይህንን ጉዳይ የሚከታተሉ ሰዎች መመደብና እነዚህ ደግሞ ተቀነባብረው የሚሰሩበት ሁኔታ መፍጠር አንዱ ተቀዳሚ ተግባር ተደርጎ ቢወሰድ ጥሩ ይሆናል።

3. ይፋ የሆኑ ቅስቀሳዎች ስለመጀመር። በያለበት የድጋፍ ኮሚቴዎችን በዚህ መልክ እንዳሳመንን ይህንን ስትራቴጂ ለማስፋፋት **በፅሁፎች ስርጭት መሰማራት** ብቻ ሳይሆን በድጋፍ ኮሚቴዎች አማካኝነት በያለበት **ህዝባዊ ስብሰባዎችን ማዘጋጀት።**

4. የህብረቱን እንቅስቃሴ በዚህ መልክ እያካሄድን ይህንን ሰነዳችንን ከኢህአፓ ዴሞክራቲክ አልፈን (ወይም ከነሱ ጋር ተወያይተን በምንደርስበት የጋራ ሰነድ አማካኝነት ከነሱ ጋር ተባብረን) ከሌሎች **የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ስብስቦች** ጋር እየተገናኙ ውይይት ማካሄድ። በዚህ መልክ የምንቀርባቸውን ድርጅቶች ሊስት ማውጣት። በዚህ ተግባር የድጋፍ ድርጅቶች በየአካባቢያቸው ይህ ሰነድ ቢደርሳቸው ይጠቅማል የሚሏቸውን ስብስቦችም ሆነ ታዋቂ ግለሰቦች ሊስት እንዲያስተላልፉ መጠየቅ።

4. ከዚህ ቀጥሎ የሚጠብቀን ተግባር ተደጋግሞ ጥሪ ሲተላለፍበት የነበረው **የሁሉን አቀፍ ጉባኤ** ጉዳይ የማዘጋጀቱ ተግባር ይሆናል። ይህ ብቻችንን የምናደርገው ሳይሆን ከሌሎች ከምንገናኛው የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ስብስቦች፣ የሙያና ሌሎች ማህበራት፣ ታዋቂ ግለሰቦችና የሃይማኖች አባቶች፣ የሴቶችና የወጣቶች ስብስቦች ተወካዮ

ች ጋር በጋራ የምናከናውነው ነገር ስለሆነ ከነዚህ ሃይሎች ጋር በምናደርገው ግንኙነት ከወዲሁ አላማችን ወደዚህ አይ
ነቱ ጉባኤና ወደ ጋራ የትግል መድረክ ለመሄድ እንደሆነ በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርብናል።

**ለ/ በረዥም ጊዜ ደረጃ ከወዲሁ የሚታሰብባቸው**

1. የህብረቱን ልሳን የመጀመር ጥያቄ። ህዝባችንን በሚያስጨንቁት ጥያቄዎች ዙሪያ ለማንቀሳቀስ ከፈለ
ግን የቅስቀሳ አርእስቶችን በጥንቃቄ ተመርጠው በነሱ ዙሪያ ግልፅና ቀጣይነት ያለው ስራ መስራት ያስፈልጋል። ትግላ
ችን የግንቦትን ቅልበሳ ተቋቁመን ከህዝባችን ድምፅ ጋር አብረው የተነጠቁትን የኢኮኖሚና ማህበራዊ አማራጮች እ
ውን ለማድረግ ስለሆነ የቅስቀሳ አርእስቶቻችን በአማራጭ ሰነዳችን ዙሪያ የተቃኙ መሆን ይኖርባቸዋል። ከነዚህ ውስ
ጥ ለምሳሌ የመሬት ጥያቄ፣ በተለይ በወጣቱ ዙሪያ ያለው የጅምላ ስራ አጥነት፣ በገጠርም በከተሞችም የመናጢ ድህ
ነት መስፋፋት፣ የአካባቢ ውድመት፣ የኤች አይ ቪ ኤይድስ፣ አድላዊ የንግድና የኢንቬስት ፖሊሲ ወዘተ ሊጠቀሱ ይ
ችላሉ።

2. በየመስኩ በተለያዩ የቅስቀሳ አርእስቶቻችን ላይ በቂ እውቀት ያላቸው ዜጎችን በትግሉ ለማሳተፍ መ
ሞከር። እንደሚታወሰው አማራጭ ሰነዳችንን ከማሰናዳታችን በፊት በየመስኩ ባለሙያዎች ተጠቁመው እነሱ ለሰነዱ
አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ተጠይቀው በርካታ ሰነዶች አዘጋጅተውልን ነበር። አማራጭ ሰነዱ ከነዚህ ምሁራን በተገኙ
መረጃዎችና ትንተናዎች ላይ ተመርኩዞ የተነደፈ ሰነድ ነው። ዛሬ ባለንበት ሁኔታ እነዚህን አማራጮች ደግመን በማ
ቅረብ መወሰን አንችልም። ከዚህ ይልቅ እነዚህኑ ባለሙያዎች ወይም ደግሞ ሌሎች ምሁራንን በመቅረብ ዛሬ በየመስ
ኩ እየተባባሰ የሄደው የህዝባችን የኑሮ ችግር እንዴትና ለምን ከኢህአዴግ ቀጣይ አጥፊ ፖሊሲዎች ጋር የተቆራኘ እን
ደሆነና አሁንም ቢሆን በግንቦት ምርጫ ወቅት ከቀረቡት ህዝባዊ አማራጮች ሌላ መፍትሄ እንደሌለ ለማሳየት መሞከ
ር ያስፈልጋል።

3. አሁን ስራችንን በውስጥም በውጭም አንቆ የያዘው ነገር የፋይናንስ ጉዳይ እንደ ሆነ ግልፅ ነው። ያለ
ንበት አዙሪት ያለ ገንዘብ መንቀሳቀስ አንችልም። ካልተንቀሳቀስን ደግሞ ገንዘብ ማግኘት አንችልም። አሁን ባለው የአ
ጠቃላይ ትጥቅ መፍታት ሁኔታ ህዝባዊ ስብሰባዎች ተደርገው በዚያ አማካኝነት ገንዘብ መሰብሰብ የሚባለው ነገር ብ
ዙም አይታየኝም። ሆኖም ይህንን ከመሞከር በስተቀር በበኩሌ ሌላ አማራጭ ያለ አይመስለኝም። ምናልባት ከድጋፍ
ኮሚቴዎች ጋር የሚደረገው ውይይት አንድ ደረጃ ሲደርስ በየአካባቢያቸው እነሱ ወጭውን እየቻሉ ስብሰባ እንዲጠሩ
ና የአመራሩ ተወካዮች እየተዘዋወሩ ገለፃ ቢያደርጉ ያዋጣ ይሆናል። በተለይ ደግሞ ሸንጎ ተደርጎ የትግል አቅጣጫችን
በውሳኔ መልክ ይፋ ከሆነ በኋላ እንዲህ አይነቱ የገለጣ ዙር ቀልብ ሊስብና ብዙ ተሳታፊ ሊያገኝ ይችል ይሆናል።

ለጊዜው በኔ በኩል ቀጣይ ተግባርን በሚመለከት የሚታዩኝ እነዚህ ናቸው። ምናልባት አንድ ነገር መጨ
መር ቢያስፈልግ ከእንግዲህ "እንሰራቸዋለን" ብለን ለምናቅዳቸው ነገሮች ሁሉ ከኛው መሃከል ወይም ከስራ አስፈፃሚ
ው ውጭ ካሉ ድጋፍ ኮሚቴዎች አባላትም ሆነ ከሌሎች ዜጎች ከተውጣጡ ሰዎች የዚያ የተባለው ስራ ተከታታዮች
አድርጎ መሰየምና ለሁሉም ስራ "ባለቤት" መመደቡ አስፈላጊ ይመስለኛል።

ነገደ
13/11/08